# <u>የወደቀው ላይነሳ ፤ ያለፈው ላይመለስ</u>

*ታሪክን ሰሪ ሰው ነው--ሰው ግን በፈለገውና ባፈተተው ታሪከን ሊቃኝ መቻል አለመቻሉ ዛሬም አነጋጋሪ ነው። ታሪክን ግን አብዮት ሊነዳው ሊያራምደው መቻሉ ላይ ግን ምንም ጭቅጭቅ ሊኖር አይችልም። የሰው ልጅ በትግሉ ታሪከን ሊመራ ሊቃኝ ይችላል ብለን እናምናለን።*

*አንዳንዶች ግን ይህን ሀቅ መገንዘብ ይሳናቸውና የወደቀውን ለማንሳት ያለፈውን ለመመለ ስ ሲማስኑ እናያለን። ከንቱ ልፋት ነው። የወደቀን ስርዓት በተለይም በሕዝብ አብዮት የፈረ ሰን ስርዓት ዳግም ነፍስ ለመዝራት መነሳት ከንቱ ነው። ታሪክን ወደኋላ ለመጎተት የሚሹ ክፍሎች ነጋ ጠባ ስለሞተውና ጊዜ ስለቀበረው ሙሾ እያወረዱ ያን የታገለውን አኩሪ ትውልድ ሲያወግዙም መስማት ተገደናል። ያሳዝናል። ያለፈውና የወደቀው የሚታዘንለት አይደለም። አብዮት የፈነዳበት ቆሻሻና አስከፊ በመሆኑ ነው። የሕዝብ ቁጣ የመጣበት ፀረ ሕዝብ ሆኖ በመገኘቱ ነው። የሕዝብን መብት ያከበረና ፍላጎቱን ያሟላ መንግስት አመፅና አብዮት አይመጣበትም። ሕዝብ በቃኝ ብሎ ተነስቶ በትግሉና በደሙ የጣለውን አገዛዝና ስርዓት ደግሞ ማንም ዳግም እስትንፋሰ ሰጥቶ ህልው ሊያደርገው አይችልም። አልፏል፤ ጠፍቷል፤ተንኮታክቷልና ። ለዚህም ነው ዛሬ ከዓመታት በኋላ ያለፈውን ስርዓትና አገዛዝ ለመመለስ ደፋ ቀና የሚሉት ዜጎች ከንቱ ልፋት አሳዛኝ ክስተት ሆኖ የሚሆኘው።*

*በሀቅ ላይ የተመሰረተ ግምገማ ከተደረገ ያለፉት ስርዓቶች ከሕዝብ መሰረታዊ መብቶች አንፃር አያሌ ጉድለቶች እንደነበራቸው ይታያል። በብሄረሰብ ሆነ በሀይማኖትና ፆታ ደረጃ ልዩነቶች ነበሩ። የየካቲት 66 አብዮት ሲፈነዳ እነዚህ ልዩነቶች ዋና ጥያቄዎች ሆነውና በስልፍም ታጅበው ቀርበዋል። የሕዝብ ፍላጎት ልዩነቶችና ጭቆናን ማስወገድ ነበርና በሁሉ ም መስክ የነበሩትን በደሎች በመቃወም ሕዝብ በጋራ ያካሄደው ትግል የሚረሳ አይደለም። ዛሬ የዱሮዎን ለመመለስ የሚገልጉ ክፍሎች ሕዝብ ያደረገውን ትግል ጥፋት በማለት እያካሄ ዱ ያሉት ጫጫታ ቢያንስ የሚያስተዛዝብ ነው። የፈረደበትን ጀግና ትውልድ በታገለና በተሰዋ አጥፊ ብለውና የስርዓቱን መበስበስና አብዮት ጠሪነቱን በመካድ በዚያ ትውልድ ላይ ዛሬ እያካሄዱት ያሉት ዘመቻ የሚያጋልጠው ራሳቸውን ነው። የአገዛዞቹን ችግር ያ ትውል ድ ሊፈታ ጣረ እንጂ ችግሮቹን አልወለዳቸውም፤ አልፈጠራቸውም ። እነ ኢሕአፓ ከመመ ስራተቸው ብዙ ዓመት በፊት የኦጋዴን፤ የኤርትራም፤ የሰርቶ አደሩም፤ የአርሶ አደሩም መሰ ረታዊ ችግሮችና ቅሬታዎች ነበሩ። ታጋዩና ተራማጁ ትውልድ ለነበሩት ችግሮች መፍትሔ ሰጥቶ ጠንካራ አንድ ኢትዮጵያን እውን ሊያደርግ ጣረ ታገለ እንጂ ሀገር ትጥፋ ብሎ በግድ*

የለሽነት አይሰሬ ፖለቲካን አልተከለም። ለዚህም ነው ዛሬ በዘያ ትውልድ ላይ ዘመቻ የከፈ ቱት ሁሉ የወደቀን ናፋቂ ሆነው የሚገኙትና ሰሚም የሚያጡት።

ያለፉትን ስርዓቶችና አገዛዞች ናፋቂ የሆኑ ሁሉ ከሕዝብ ጎራ በአቅዋማቸው ተመንጥረው የወጡ ናቸው። አልተረሳምና ሀቁ የሚነግረን በአፄው ዘመን በብሄረሰብም ሆነ በሀይማኖት ደረጃ ምንም እኩልነት አለመኖሩን ነው። በዘመነ ደርግም ቢሆን አፋዊውን ልፈፋ ስንተው የስርዓቱ ሀቅ ሁለገብ ጭቆና ነበር። ወያኔም ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ሀሉንም ሀይማኖችን በጫማው ስር ማስገባት ነው ተልዕኮው የሆነው ። ይህንን ነው ዛሬ አማኞች/ዜጎች እየተቃወ ሙ ያሉት። ይህን ሕዝባዊ ትግል በመደገፍ ፈንታ ጊዜ ያለፈበትን ከፋፋይ አቅዋም ይዘው ኡኡታና ቡታ የጀመሩትን ዜጎችንም እረፉ ዝም ብሉ ማለትም አስፈላጊ ሆኗል ። ኢትዮጵ ያ የአማራና የክርስቲያን ሀገር ብቻ ሳትሆን የእስላሞችም፣ የልዩ ልዩ ብሄረሰቦችም ሀገር ናት ። የኢትዮጵያዊነት ትርጉሙና ይዘቱ አማራነትና ከርስቲያንነት ብቻ አለመሆኑ በየካቲ ት 66 አብዮት ያበቃለት በመሆኑ ዛሬ የታሪከን ጎማ ወደ ኋላ ወስዶ ለወያኔ በሚጠቅም ልፈ ፋ መጠመዱ ለሀገራችን አይጠቅምም። ዛሬ ምን ያህል ኡኡታ ብናሰማ ያ የወደቀ የፊውዳ ል ስርዓት ከነቆሻሻው ከቶም የሚመልስ አይደለም። አልፏል፣ አክትሟል። የደርግም አረመኔ አገዛዝ ለተባባሪዎቹ ቢናፍቃቸውም ተቀብሯልና አይነሳም። በሕዝብ ትግልና ደም የተገኙ ድሎች የሚሰረዙ አይደሉም። ዛሬ ታሪከን ከሀዲዎች ምንኛ ቢንጫጩ ያ የታገለን ትውልድ ታሪክና ተጋድሎ ክደው ሊወነጅሉ የሚቃጡት ተልዕኮ የሚሳካና አድማጭ የሚያገኝ አይደ ለም። የበሰበሱ ስርዓቶችን ጉድለትና ሐጢያት በታገላቸው ትውልድ ላይ መጫንም አያዋጣ ም። የነበረን በደልና የመብቶችንም ጥሰት አልነበረም ብሎ መካዱ ለምንፈልገው ትግልና ለውጥ የሚጠቅም አይሆንም።

የታሪከን ጎማ ወደ ኋላ ዘውሮ የነበረን ወይም ሕዝብ ያልፈለገውን ትላንትን የዛሬ እውነታ ማድረግ አይቻልም። የተወሰኑ ክፍሎች ምንኛ ቢመኙም ቢንጫጩም የአፄው ዘመን ስርዓት ና አስተሳሰብና አገዛዝ መቼም ተመልሶ አይስፍንም። የዴሞክራሲና የእኩልነት ነፀብራቅ አልነበረምና፣ የበደልና የስቃይ ስርዓት ነበርና። የደርግን ስርዓት የሚናፍቁ ደግሞ ነፍሰ ገዳዮችና የሽብር አባወራዎች ናቸው። ትውልድን ያጠፉ፣ አረሜኔን ስርዓት የሚያደንቁ አውሬዎች እንጂ ሰዎች የሚባሉ አይደሉም ። ያለፉት ስርዓቶች በሁሉም መስክ የሕዝብን መብትና ፍላጎት ያከበሩ አልነበሩም። ከሀገር አንድነት ፍላጎታችን ብንነሳ ለምሳሌ የአፄው ም ሆነ የደርጉ ስርዓቶች ሀገር ወዳድ ነን ቢሉም አቅዋማቸውና ድርጊታቸው ግን የሕዝብን አንድነት የጎዳና ያጋለጠ ነበር። ይህን ሀቅ ተረድተው መፍትሔ የፈለጉት ተራማጆችና ኢሕአፓዎች ለነበረው ችግር ተጠያቂ ሳይሆኑ የችግሩ ወላጆች ስርዓቶች ነበሩ። ለበሽታው ሐኪሙን ተጠያቂ ማድረጉ ስህተት ነው። ወጣም ወረደም ግን ሕዝብ መረረኝ ብሎ የጣለ

ውን አቅዋም፤ፖለቲካና አገዛዝ መልሶ ለማስፈን መዳከሩ ከንቱ ነው። ሕዝብ የወያኔን ተንኮ ልና ሴራ ተረድቶ ዛሬስ በጋራ ሊታገል ሲነሳ ሕዝብን በብሄረሰብ መከፋፈል ወያኔያው ወንጀል ነው። ሕዝብ ዛሬ ወያኔ ሀይማኖትን ለክፍፍል ሊጠቀምበት ሲዋደቅ ተረድቶ ሀይማ ኖት የግል ነው ሀገር ግን የጋራ እያለ ባለበት ኢትዮጵያ የዚህ የዚያ ሀይማኖት ብቻ ሀገር ናት ብሎ መለፈፍ ወያኔን መርዳት ነው። አዎ ታወቀም አልታወቀም፤ ተወደደም ተጠላም ወያኔ መሆን ነው ።አዎ ቢጎረብጥም ይህ ነው ሀቁ ።የዱሮውን ናፋቂ ክፍሎች ለኢትዮጵያ አይጠቅሙም።

ቡቱቶ ልብስ አይደለም። በትግልና በደም አውሬ ስርዓቶችን፤ ፀረ ሕዝብ አገዛዞችን ጥለናል ። ለኢትዮጵያ ለሕዝቧ የሚጠቅሙ አልነበሩምና። ዛሬ ተመልሰን በራሳችን ላይ ቀንበር ጭነ ን ህልውና ልንሰጣቸው ከቶም መቼም የሚታሰብ መሆን የለበትም። በአንፃሩ ደግሞ የደም ዋጋ ከፍለን ያገኘናቸውን የትግል ተመክሮውች በጅምላ ውደቅ የሚያደርጉትንም ጆሮ የምንሰጣቸው ልንሆን አንችልም። በትግሉ ሜዳ ላይ መቼም ሳይገኙ ወይም ዛሬ ከትግል ርቀው ግና ምሁር ልሂቅ በሉን ብለው ያን የታገለውን ትውልድ በዚህም በዚያም የሚያብጠ ለጥሉ ሁሉ ለሀገር የሚጠቅሙ አይደሉም። ለሀገራችን ድቀትና መከራ ተጠያቂዎች ስርዓቲ ቹ መሆናቸውን ሽፍነው የታገሉትን ዜጎች ይደቁሳሉና ተልዕኮአቸውና ሚናቸው ሕዝባዊ ሳይሆን ጎጂና አሳፋሪ ነው። ታጋይ ድርጅቶችን በመከፋፈልና በመጉዳት መሰማራት ነው። ይህን ደግሞ ያነውና እያየነው ያለ ነው። ሐሳዊ መሲሆቹ በርክተዋል። ጭምብላቸው ብዙ ነው። አወናባጆችን ስናይ የባጀን ቢሆንም ነጋ ጠባ በአዲስ ስምና ሽፍንፍን ብቅ እያሉ ያጠቁናል። ልናብር ስንል በብሄሰረሰብም በሀይማኖትም ለመከፋፈል ያጮሁብናል። ለማበር ስንነሳም በደፈናው ህብረት፤ ጥምረት ሽግግር ብለውም ድንግርግር ዝብርቅርቅ ያደርጋሉ። ዜጎችን ይከፋፍሉ እንጂ ዘላቂ ጉዞ የላቸውም። ይበታተናሉ ። ስንቶቹን አሰተናግደን ሸኘተ ናል? ስንቱ ተቃዋሚ ድርጀት ተብዬ ብቅ ብሎ ሳይውል ሳያድር ተሰነጣጥቆ ኢምንት ሆኗ ል? ስንቱ ተቃዋሚ በጥብቅ ሲመረመር የባዕዳን መሳሪያ ሆኖ ተጋልጧል? ስንቱስ አወቅኩ ባይ ተቃዋሚ ነኝ ምሁር ነኝ ባይ በአጭር ጊዜ ሰልፉ ከሆዱ ጋር መሆኑ ታውቆበታል?

ለዚህም ነው የትላንት ወንጀለኞች፤ ትላንት ሕዝብ ሲታገል አንቀላፊ የነበሩ ማፈሪያዎች፤ ዛሬ ከወያኔ ያደሩ ዘመናዊ ባንዳዎችና ሆዳሞች፤ ያለፈና የወደቀ ስርዓትን ናፋቂዎች፤ ትምክተኞችና ጠባብ ብሔረተኞች፤ የባዕዳን ቅጥረኞች፤ የሻዕቢያ ሎሌዎች፤ ከፋፋይ አንጃዎች፤ አስመሳዮችና የድል አጥቢያ አርበኞች ሁሉ የነገን ኢትዮጵያን አምጪና ገንቢ ሳይሆኑ ሀገርን አጥፊዎች ሆነው የተሰለፉት ። ለኢትዮጵያ ቆምን ቢሉም አቅዋማቸው ሁሉ ሀገርን የሚከፋፍልና የሚጎዳ ነው። የሕዝብን አንድነት በተጨባጭ ይፃረራሉ። የድርጅቶችን

ትብብርና ቅንጅትን  በገቢር ይቃወማሉ፡፡ እስላም ክርስቲያን ፤አማራ-ኦሮሞ- ትግሬ ወዘተ ብለው ሕዝብን ይከፋፍላሉ፡፡ የኢትዮጵያን አንድነት በክፍፍሏ መሰረት ላይ ይፈልጉታል፡፡ በመሆኑም ፖለቲካቸው ገንቢ ሳይሆን አጥፊ ነው፡፡ ለማንነታቸው አንዱ መለያ ደግሞ ነጋ ጠባ በማያወላዳ ደረጃና በፅናት ፀረ ወያኔ  በሆኑ ድርጅቶች ላይ ፀያፍና አፍራሽ ዘመቻ ማካሂዳቸው ነው፡፡ ወደዱም ጠሉም ሚናቸውና ጠቀሜታቸው ለወያኔ መሆኑም ይታያል፡፡ መርዶው ግን የወደቀው አይነሳም፤ ከታሪክ ትቢያ የተጣለውም ሰማይና መሬት ቢጋጠሙም ከተወረወረበት ወጥቶ ነፍስ አይዘራም የሚል ነው ፡፡ የነገይቷ ኢትዮጵያ ትላንት ገማ ገለማ ብለንና ደም አፍሰን ባስወገድነው ፀያፍ ሁሉ ላይ ሊመሰረት አይችልም፡፡ ኢትዮጵያ አንድነ ቷን ጠብቃ በዴሞክራሲ መሰረት ላይ ልትቆም የምትችለው የትግል ቅርሷን አክብራ፤ ደም የተከፈለበትን ተመክሮ አቅፋ አንጂ ያለፈውንና ሕዝብ የጠላውን አቅዋምና ቅርስ ላድስ ብላ

ሊሆን አይችልም፡፡